# በሠላሟ ተመራጭ አገር

በቀለ ግርማ

ሠላም ሲባል ቋንቋው የየተናጋሪው ልዩነት ካልሆነ በቀር ግብሩ ግን የምድራችንን ሰብዓዊ ፍጡራኖች አንድ አድርጎ የሚገዛ ሀሳብ ነው። የሰው ልጆችን በየቋንቋቸው ያነጋግራቸዋል፣ ያወያያቸዋል፣ ያዘምራቸዋል። ከዚህ አለፍ ሲልም ስለሠላማቸው ወደየአምላካቸው ያስፀልያቸዋል።

ዛሬ…ዛሬ ሠላምን የሚነሱ በርካታ የሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ክስተቶች በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ይሰማሉ፤ ይስተዋላሉ። ከእነዚህ ክስተቶች መካከል የሰው ልጆችን ሠላም በተለይ ከሚነሱ ሁነቶች መካከል የእርስ በርስ ጦርነቶች፣ የአገሮች በሌላ አገራት ጣልቃ ገብነት አሊያም ድንበር ተሻጋሪነት ወይም ወረራ፣ ወረርሽኝ ይጠቀሳሉ። ከአንደኛው አገር ወደ ሌላኛው አገር የሚዛመቱ በሽታዎች በተለይ በምጣኔ ሀብት አቅማቸው ዝቅ ባሉት ላይ ቢብስም ዋጋን ያስከፍላል። የአገራቱን ሠላምም ያናጋል።

እንደ ውኃ መጥለቅለቅ ወይም ጎርፍ፣ ማዕበል የአውሎ ነፋስና የምድር መናወጥ ከብዙ በጥቂቱ ተጠቃሾች ናቸው። ችግሮቹም በተከሰቱበት አገር ብቻ የሚያበቁ አይደለም። የግንኙነት ሰንሰለታቸው ሰፊና ጠንካራ በመሆኑ በአንድ አገር ለምሣሌ እንደ ሱናሚ ያለ አስከፊ አደጋ ሲከሰት የጉዳቱ ወሰን አሊያም ጥላው ሩቅ ይጓዛል።

ሌላው የዓለማችን የዘመናችን የሠላም ጠንቅ በመሆን የተለያዩ አገራትን በማመስ ላይ ያለው የሽብርተኝነት ሰፊ መረብ ነው። ምድራችን አንዳንድ ጊዜ የዛፍ አሊያም የእፀዋት እሾህ ብቻ ሳይሆን የሰዎች አሾህንም ታበቅላለች ያሰኛል።  ምክንያቱ ደግሞ የዓለማችን የመኖር ህልውና ሠላም ትልቁን ሥፍራና ቀዳሚውን ደረጃ አለያም ወሣኙን ቦታ ይይዛል። ታዲያ የሠላም ዋጋ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያልተረዱ ወይም ደግሞ የሰዎችን አሊያም የአገራት ሠላም ገንዘብ የማይመስላቸው ፀረ ሠላም ኃይሎች በዓለማችን ከስንዴ መሃል እንክርዳድ እንደሚባለው ሆነው ይኖራሉ። ለዚህም ነው ምድራችን የእፀዋት አሊያም የዛፍ እሾህ ብቻ ሳይሆን የሰውም እሾህ ታበቅላለች የሚባለው።

የዓለማችን ነዋሪ ሕዝብ ስለሠላም ሲባል የማይፈነቅለው ድንጋይና የማይቀምመው መድኃኒት ወይም ደግሞ የማይዘይደው የመፍትሄ ዓይነት የለም። ለምሣሌ በአንዳንድ አገራት የእርስ በርስ ግጭት አይሎ በከፋ ደረጃ ይደርስና ጦርነት ሲቀሰቀስ ሌሎች አገራት በተጠለሉበት አካል ሥር ተሰባስበው የሠላም አስከባሪ ኃይል በማዋጣት ይልካሉ።

ሠላም ከአንድ አገር በመጥፋቱ ተጎጂው ከማንም በላይ ሠላማዊው ሕዝብ ነው። ለአብነት እንደ ህፃናት፣ አቅመ ደካሞችና ህመምተኞች ይጠቀሳሉ። በዚህ ረገድ ሠላማቸው ለብዙ ጊዜ ተናግቶ እርስ በርስ ጦርነት የከፋ እልቂት ያጋጠማቸው አገሮች ከየአህጉራቱ መጥቀስ ይቻላል።

በተለይ በዚህ በያዝነው የ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተከሰቱ አሰቃቂ የሚባሉ እልቂቶች ወይም ጦርነቶች የተከሰተባቸው አገሮች ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ ሊቢያና ሶሪያ ያሉ አገራት በማሳያነት ይጠቀሳሉ። ስለ ሠላም ውድ ገንዘብነት የእነዚያ አገሮች ዜጎች ቢናገሩት እጅግ ከባድና ጥልቅ ስሜት ሰባሪ ሃዘንን ያሸክማል።

በዚህ በኩል ታዲያ ለማሳያነት በወቅታዊነታቸው ያነሳናቸውን አገሮች አየን እንጂ የእርስ በእርስ ጦርነት በተለይ አፍሪካና አፍሪካውያንን በልዩነት የሚያስጠራ እስከ መምሰልና እስከ መሆንም የታሰበበትና የታመነበት አጋጣሚ መኖሩ ይታያል። ነገር ግን ከዚህችው የአፍሪቃ አህጉር ስለ ሠላም ታላቅ መስዋዕትነት እየከፈሉ ያሉና ያለፉ ድንቅና ብርቅ የአህጉሩ ልጆች ተገኝተዋል።

በዚህ ረገድ አገራችን ኢትዮጵያ ስለ ሠላም በተከፈሉ ታላላቅ መስዋዕቶች አውድ የአፍሪካ አህጉር ግንባር ቀደም ወይም ፊታውራሪ በመሆን ዓለም አቀፍ እውቅናና ይሁንታን አግኝታለች። አገራችን ለሠላም ዘብ የቆመችው ዛሬ ብቻ አይደለም። ከራሷ ባለፈ በቀደምት አባቶቻችንም በኮሪያና በኮንጎ ህያው የታሪክ አሻራ ያስቀመጠች የአፍሪካና የአፍሪካውያን ብርሃን ናት። የሠላምን ዋጋ ኢትዮጵያውያን በእጅጉ ያውቁታል። አገራችን በርካታ ጊዜ ሠላሟን የሚነሱ ኃይሎች መተንኮሳቸው ይቀራል ማለት አይደለም።

የዜጎች በሠላም ወጥቶ መግባት የሕዝቦች በሥራ ላይ በሠላም መሰማራት በጥቅሉ የአገራችንን ሠላም በፍፁም የማይሹ ኃይሎች ለሠላማዊ ጉዟችን እንቅፋትና መሰናክል ሊያስቀምጡ ሲንቀሳቀሱና የሃሳብ ጋሬጣቸውን ሊጋርጡ ከማሴር ተቆጥበው አያድሩም። ዳሩ ግን ‘ተንጋሎ ቢተፉ ተመልሶ ባፉ´ የሚባለውን ብሂል ዓይነት ሆነና የሚያስቀምጡት ጋሬጣ ራሳቸውን እየወጋ ሳያስኬዳቸው ሲቀርና የሚያጠምዱት ወጥመድ ራሳቸውን እያጠመዳቸው ሲያስጨንቃቸው እነርሱ ሊያደፈርሱት የሚጥሩት የሠላም አየር አልሞከር ሲላቸው ሕዝብን መንግሥትንና አገርን ከመኮነን ባሻገር ተጠያቂ ለማድረግ ያሸረግዳሉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የሚሆነውን፣ የሚሻለውን፣ የሚበጀውንም ከእነዚህ ፀረ ሠላም ኃይሎች በበለጠና በቅድሚያ ተረድቶታል፤ ያውቀዋል። ሁሉንም እየታዘበና ሚዛናዊ ፍርዱን እየሰጠ አሳይቷል።

ሠላም መፍጠር ከራስ ይጀምራል። ግለሰቦች ስለሠላማቸው ማሰብ አለባቸው። ማንም ሰው በተለያየ ምክንያት ሠላሙን እንዳያጣ አበክሮ መቆም አለበት። ሠላም የሁሉም ውድ ሀብት ነው። ሠላም ከሌለ ወጥቶ መግባት መሥራት፣ መማር እንዲሁም መኖርም አደጋ ላይ ይወድቃል። ሠላምን ከማንም በበለጠ የትኛውም ዜጋ አሊያም ሕዝብ በሚገባ ይገነዘባል። በመሠረቱ ስለሠላም ቢሰበክ፣ ቢተነተን ወይም ደግሞ ቢዘረዘር ምንጊዜም ቢወራ ጠቃሚ ነው።

ሠላም የህልውና መሠረት፣ ሠላም የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ዋነኛ መሠረት፣ ሠላም የልማት መሠረት የሆነ በጊዜና በገንዘብ በምንም ሊተመን የማይችል ሀብት ነው ዘመናት በሰው ልጆች አሊያም በየትውልዶች የአኗኗር ቅብብሎሽ ውስጥ የራሳቸውን አሻራ አስቀምጠው ያልፋሉ። ትውልድም ቢሆን እንደዚያው የየራሱን አሻራ ማስቀመጡ እውነት ነው። ለዚህ የዘመንና የትውልድ አሻራ ማረፍ ታዲያ በሠላሙ ጊዜ የበለጠ ሲሰራና ሲያሰራ ሠላም ባልተገኘበት ወይም ሠላም በጠፋበት አጋጣሚ ደግሞ የትውልዶችና የየዘመኑ አሻራዎች የተጓተቱባቸውን የአገራችንን እውነታዎች በብዛት እናገኛለን።

በዚህ ረገድም አገራችን ነገ ሰልጥኖና በልጽጎ ለመታየት የነበራት የትናንቱ የአፄዎቹ በተለይም የ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ላይ የነበሩት መሪዎች ራዕይ በግፍና በእብሪት በተነሳ የቅኝ ግዛት ተስፋፊነት አባዜ በተፀናወታቸው የዘመኑ የአውሮፓ መንግሥታት አገራችን በነበረችበትና ባላት ኋላ ቀር ወይም ያልሰለጠነ አሊያም በሂደት ላይ በነበረ ጉዞ የተያያዘችውን የዕድገት ጉዞና ተስፋ አቁማ ላልተፈለገ የግፍ ወራሪዎች መከላከል ወይም ደግሞ አገርን ከወራሪ ባዕድ ለማስለቀቅ ወደጦርነት ማምራቷ ዛሬም ድረስ ይታወሳል።

ያንን ጊዜ ዛሬ ላይ በኋሊዮሽ ትዝታ ሲታይም ቢሆን ሲታወስ በዜጎች ልቦና የሚነሱ በርካታ ቁጭቶች እንዳሉ ማሰብ ይቻላል። በዚያን ወቅት ከውጪም ከውስጥም ሠላም ሰፍኖ ቢሆን ኖሮ የተጀመሩት የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች በእንጪጩ ወይም በሀሳብ ጅምር ባይቀሩ ኖሮ ለዛሬው ይህንን መሰል የዕድገት ቅብብሎሽ ለዚህ ዘመንና ለዚህ ዘመን ትውልድና አገር መሪዎች በምን ያህል እገዛ ሊኖረው ይችል እንደነበር መገመት አዳጋች አይሆንም።

ስለዚህ የዚህ ዘመን ትውልድ አሁን ያለው አገር ተረካቢ የነገን በትናንት መነጽር እያሻገረ የሚመረምረው፣ የሚያነፃፀረውና የሚተነብየው ይህ ትውልድ የሠላምን ታላቅነትና ልዩ ሀብትነት በውል እየተረዳና እየተገነዘበ መጥቷል። ፀረ ሠላም ኃይሎች የሚያስቀምጡለትን ወጥመድ በተለየ ንቃትና የኃላፊነት መንፈስ ሊከታተልና ሊጠብቅ እንዲሁም ወደዚህ የሠላም አደፍራሽ ዓይነት ጉዞ ለመቀላቀል የሚያስቡ ካሉ መልሶ መላልሶ የሠላምን ዋጋና ጠቀሜታ በማሳየት ወደ ሠላማዊ ጉዞ መስመር እንዲገቡ የመስራት ታላቅ አደራም ተጥሎበታል። የፀረ ሠላም ኃይሎችን ኋላ ቀር ብሂል በመሰረዝ ዜጎች ሁሉ ስለ ሠላም ሲሉ ምን መሆን፣ ምን መስራት፣ ምን ማሰብ እንዳለባቸው ግንዛቤ ለመፍጠር ጊዜ መውሰድ አያስፈልግም። ሌላ ቀርቶ በአንድ መጋቢ አውራ መንገድ ላይ ሁለት

ተሽከርካሪዎች ተጋጭተው መንገድ ሲዘጋ ያለውን መረበሽና የጊዜ ብክነት በንፅፅር ማየቱ በቂ ነው። እንግዲህ የሁለት ተሽከርካሪዎች ግጭት እንኳ ለመንገድና ለመንገደኞች ደህንነት የሠላም ጉዞ የጊዜ ብክነት አሉታዊ ጎን ካለው የፀረ ሠላም ኃይሎች እንቅስቃሴ ታስቦበት የሚደረግ አደጋ ስለሆነ ምን ያህል መሰናክል ሊሆን እንደሚችል ተገንዝቦ በየትኛውም መልኩ በየትኛውም ቦታ በማንም ይሁን በምን የሠላምን አየር ሊያደፈርስ የሚችል ትንሽ የሚባል ነገር የለም።

ሆኖም ትንሽ ፍንጭ እንኳ ጥርጣሬ ሲኖር ለሚመለከታቸው አካላት በፍጥነት የተለመደ የነዋሪው ኅብረተሰብ የማይዘነጋ ኃላፊነት ሆኖ መቀጠል ያለበት ጉዳይ ነው። በአገራችን ትምህርት ቤቶች ከመዋዕለ ህፃናት እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ማለትም ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች፣ በየዕምነት ተቋማቱ በክርስትናም ይሁን በእስልምና ማለትም በየአብያተ ክርስቲያናትና በየመስጂዶቹ ስለሠላም ይሰበካል፣ ስለሠላም ይዘመራል።

ሠላምን የማያውቅ ባለንፁህ አዕምሮ ሰብዓዊ ፍጡር አለ ለማለት ይከብዳል። ስለሠላምና ሠላምን ማወቅ አንድ ጉዳይ ሆኖ ሠላምን ያለመፈለግ የሠላምን ትልቅ ዋጋ ያለመገንዘብ ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው። እናም በብዙዎች ደምና ድካም የተገኘውን ሠላም ለማጥፋት መቋመጥ ከእብሪትም ካለማወቅም ብቻ ሳይሆን ከሰይጣናዊነት የሚመጣ ከንቱ ድርጊት ነው።

አሸባሪዎች ምንጩ ከየትና ከማን እንደሆነ በማይታወቅ ሀብትና ንብረት የሽብር ተግባራቸውን ለማስፈፀም የ<u>ንፁኃንን ህይወት በግፍ</u> <u>ይቀጥፋሉ</u>። የንፁኃን ደም ይፈሳል። ንፁኃኖች ከህፃን እስከ አዛውንትና አቅመ ደካሞች ከጤነኞች እስከ ህመምተኞች ህይወታቸውን በከንቱ ይገብራሉ። ሽብርተኞችና ፀረ ሠላም ኃይሎች ከርቀት በሚቆሰቁሱት እሣት የሚለበለቡትና የሚቃጠሉት ምንም የማያውቁት ንፁኃኖች ናቸው።

አገራችን ኢትዮጵያ ከሕዝቦቿና ከመንግሥት በዚህ በሽብርተኞች የማፅዳት ሥራ ዙሪያ ከባድና ውስብስብ ችግር ውስጥ እስከምትገባ ጊዜ ድረስ መጠበቅ የለባትም። ሳይቃጠል በቅጠል ነውና። የአገርንም ሆነ የዜጎችን ሠላም ለማደፍረስ የሚንቀሳቀሱ ፀረ ሠላም ኃይሎች ተይዘውና የአገሪቱ የህግ አግባብ በሚፈቅደው መሠረት ተገቢ ፍርድ መቅረብና በአፋጣኝ የእጃቸውን መቀበል አለባቸው።

ሕዝብና መንግሥት በተለይም በሕዝብ ይሁንታ የተመረጠና አገርንና ሕዝብን የሚያስተዳድር መንግሥት የዜጎችን ሠላም የማስጠበቅ የመጀመሪያ ኃላፊነትና አደራው እንዲሁም ህገ መንግሥታዊ መሠረት ያለው ታላቅ ግዴታው ነው። የሠላምን ሀብትነት ቢያውቁም ለግንዛቤው ደንታ የሌላቸው ጥቂት እንክርዳዶች ዓላማቸውን ትተው ወደጽሞናዊ፣ ሠላማዊና ሕዝባዊ ፍቅር አገራዊ ራዕይ ከሚታያቸው ወገኖቻቸው ጎራ ቢሰለፉ መልካም ነው። በፅኑ መሠረት ላይ የተገነባና የታነፀ ሠላም

ይዘው መኻዝን የሚያዳብሩበት ልቦና ቢኖራቸው እያሉ ከመመኘት ባለፈ ሠላም ፈላጊውና ሠላም ወዳድ ሕዝብ በውልና በወጉ ሊያስረዳቸው ሁሌም መዘጋጀት አለበት።

እነርሱ የሚፈልጉት ሠላም የትኛው ዓይነት ይሆን? ብለን ስንጠይቅ የተሰራን ማፍረስ የለማን ማጥፋት አልፎም ተርፎም ንፁሁንና ክቡሩን የሰው ልጆች ህይወት በጅምላ ማጥፋትና ደም ማፍሰስ ሆኖ እናገኘዋለን። የተነሱለትን ዓላማ ፍፃሜውን እንኳ በውል ሊያስገኝ የሚችለውን ትርፍና ኪሳራውን በወጉ ለይተው አያውቁትም። ለትንሽና ለማይረባ ለማይጠቅም ገንዘብ አንዳንድ ጊዜ ምንም የማያውቁትን ዜጎች ለሠላም አደፍራሽነት ወንጀል በመገፋፋት በሽብር ተግባር ላይ እንዲሰማሩና ካልሆነ እንኳ መጨረሻቸው አጥፍቶ መጥፋት እንዲሆን ያነሳሷቸዋል። የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ካላቸው ፍላጎትም ይሁን ጉጉት የተነሳ ወዳላሰቡበት የጥፋት ወጥመድ በመግባት ለከፋ ሥቃይና ኪሳራ ብሎም ለህይወታቸው መጥፊያ የሚዳረጉትን ንጹኃኖች የት የለሌ ናቸው። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያም ትሁን ሌሎች አገራት ዜጎቻቸውን በጠበቀ የሠላም መሠረት ላይ ማነፅ ይገባቸዋል። በእርግጥ አገራችን ስለሠላም ከራሷ ባለፈም ለጎረቤት አገሮች ሠላም አበክራ ትሰራለች። ዜጎቿን ጭምር በወታደራዊ አስተዋፅኦ በማሰለፍ በግንባር ቀደምነት እየሰራች ትገኛለች። ስለኢትዮጵያ የሠላም ወዳድነትና ሠላማዊ ልማት ሰባኪነትና ተግባሪነት ዓለም ባንድ ድምፅ ይመሰክረዋል። ይህ ሆነ ተብሎ ግን የራሷን የውስጢ ሠላም መጠበቅ ለአፍታም ያህል ቸል ማለትና መዘንጋት አያስፈልግም። መንግሥት እንደ መንግሥት ኃላፊነቱን በመራጩ ሕዝብ የተሰጠውንና የተጣለበትን አደራና ግዴታ የመወጣት ጉዞ ፍሬው ይጠበቅበታል። ከአገር ውጪ ላሉ ጎረቤቶቿ ሠላም አልፎም ስለ ዓለም ሠላም መከበር በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ መንገዶች የምትሰራና የምትደክመዋ አገራችን ኢትዮጵያ |የራሷ አሮባት የሰው ታማስላለች´ ይሉትን ዓይነት ብሂል ማስተግበሪያ አሊያም የጥቂት ጋጠ ወጦችና ፀረ ሠላም ኃይሎች መፈንጫ ሜዳ ለመሆን የተመቻቸ አገር መሆን የለባትም።

ፀረ ሠላም ኃይሎች ከውጭ በርቀት ሆነው በምፅዋት ያገኙትን ገንዘብ ለአገራቸው ምድር ማልሚያ ቢያውሉት ይበጃል እንጂ እንዴት ለፀረ ሠላም ግብር ማስፈፀሚያ፣ ለወገኖቻቸውና ለአገራቸው መጥፊያ ሊያውሉት ይፈልጋሉ? እውን እነዚህ ፀረ ሠላም ኃይሎች እንደዚህ በርቀት በተልዕኮ ሆነው ሲያስፈፅሙት የነበረውን ሕዝብና አገር እንበጅሃለን፣ እኛ እንሻልሃለን፣ እናስተዳድርሃለን፣ እኛ ሠላም እናመጣልሃለን ብለው ዛሬም ሊነግሩትና ሊሰብኩት ሊያሳምኑት ይሞክሩ ይሆን? ግን የእነርሱ ሠላም ምን ዓይነት ይሆን? የእነርሱ የሠላም ትርጉም በየትኛው መዝገበ ቃላት መፍቻ ያገኝ ይሆን? ንፁኃንን በማሸበርና በማፋጀትና የሚያመጡት ሠላም ምን ማለት ይሆን?

የሕዝብን ሠላም እንኳን በቅርበት ሆኖ ይቅርና በርቀት ሆኖ የፀረ ሠላምነት አጀንዳቸውን ሲያስይዙና ያለዚያም ምንም ዓይነት ዓላማ የሌላቸው ስለመሆናቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ እየታወቀና የሠላማዊ የትግል አማራጮችን ወደ ጎን በመተው የንፁኃንን ደም የሚያፈሱ ፀረ ሠላም ኃይሎችን

ከምንጊዜውም በበለጠና በላቀ መልኩ ተዘጋጅቶና ተደራጅቶ መጠበቅ የሕዝብና የመንግሥት ልዩ የቤት ሥራ ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ ለመላው አፍሪካውያን ተምሣሌትና ዓርማ የሆነችበትና የምትታወቅበት ለሠላም በምትከፍለው ዋጋ ነው። የኢትዮጵያ ሠላም አስከባሪ በተሰማራበት አገር ሁሉ የሚያሳየው ኢትዮጵያዊ ሞራልና ሥነ ምግባር ዓላማችንን በእጅጉ ያስደንቃል። በተባባሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤትም ይሁን በአፍሪካ ህብረት የሚሰጠውን ግዳጅና ኃላፊነት ከሚጠበቅበት በላይና ከተሰጠው ግዳጅም በማለፍ ስለ ሰብዓዊ መብትና ክብር ስለ ሰው ልጆች ሁለንተናዊ አስፈላጊ ነገሮች ሲሰራ የአገሪቱን ስምና ነባር ዝና በሰንደቅ ዓላማዋ ኩራት ገልፀውታል።

ኢትዮጵያ በሠላም የማስከበር ተልዕኮ ውስጥ አለችበት ማለት እውነትም ለዚያች ሠላሚን ላጣች አገር ዋስትና አገኘች ማለት ቀጥታ ትርጉሙ ነው። ይህ ደግሞ አሁን በቅርቡም እዚሁ ጎረቤታችን በኦፊሴላዊ መንገድ ነፃነቷን ለተቀዳጀችው አገር ደቡብ ሱዳን የታየ ግልጽ የሠላም ማስከበር ተግባር ነው።

የደቡብ ሱዳን ከሱዳን ከተገነጠለችና ነፃ ከወጣች በኋላም ቢሆን በነዳጅ ሀብቷ በምትታወቀው የአቢዬ ግዛት ያለው ሁኔታ ለሁለቱም ወገኖች ሠላም የሚሰጥ ሁኔታ ስላልነበረ በዚያ ሥፍራ ለሠላም ማስከበር ዋስትናውን እንድትወስድ ኃላፊነቱን የተሸከመችዋ አገር ከየትኛውም አፍሪቃዊ አገር ቀዳሚዋ ኢትዮጵያ ናት።

እናም የእነዚህ ሁለት አገሮች ማለትም የሱዳንና የደቡብ ሱዳን ሠላም በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሠላም አስከባሪ ኃይል ብርቱ ጥረትና ለሁለቱም ወገኖች ባለው ቀናዒነትና በጎ አሳቢነት የሠላማቸው ሁኔታ በእጅጉ ተሻሽሏል። አስተማማኝ ሊባልም ይችላል። ዛሬ…ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ በዓለማችን ታላላቅ የስብሰባ መድረኮች ሁሉ በብዙ ገንቢ ገፅታዎቿ ትነሳለች። ምሣሌ ተደርጋም ትወሳለች። እንዲያውም ድንቁና ባለ ራዕዩ መሪዋን አቶ መለስ ዜናዊን ምክር በመጠየቅና በመተግበር በልዩነት ተጠቃሚ የሆኑ አገሮች መኖራቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው።

እንግዲህ ኢትዮጵያ ስትነሳና ስትጠራ ሠላም የማይቀር ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ የሠላም ዋስትና የሠላም ጓዳ የሠላማውያን መኖሪያ ብቻ ሳትሆን የሠላም ምንጭና መገኛ ልዩ አገር ናት። በሠላሚ ተመራጭና ቀዳሚ የመሆኗን ያህል ምንም ዓይነት የሠላም እጦት እንከን እንዳያጋጥማት ጠንክሮ አበክሮና ሳይዘናጉ መሥራት የእያንዳንዱ ዜጋ፣ የመንግሥትና የአገሪቱ ርዕሰ አጀንዳ መሆን አለበት። ሠላም ለኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ይሁን!